STAY SAFE MN



# የ COVID-19 ክትባት መሰረታዊ መረጃ

## የ COVID-19 ክትባቶች አስተማማኝና የሚሰሩ ናቸው።

ክትባት የሚዘጋጀው በሽታዎችን እንዲከላከል ታስቦ ነው። የCOVID-19 ክትባቶች ለሰውነትዎ የCOVID-19 ቫይረስን እንዴት ለይቶ እንደሚያውቅና እንደሚከላከል ያሳውቆታል። የCOVID-19 ክትባቶች በCOVID-19 ሊያስይዙዎ አይችሉም። የCOVID-19 ክትባቶች እርስዎን ከCOVID-19 በሽታ በመከላከል ረገድ በጣም ጥሩ ናቸው። ከተከተቡ በኋላ በCOVID-19 የሚታመሙ ከሆነ በከባድ የመታመም ወይም ወደ ሆስፒታል የመሄድ እድልዎ አነስተኛ ነው።

**የ COVID-19 ክትባቶች ለአስቸኳይ ጊዜ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ፍቃድ ከማግኘታቸው በፊት በተለያዩ ቡድኖች ላይ በጥንቃቄ ተሞክረዋል።** በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ጥቁሮች፣ ላቲኖች፣ አሜሪካውያን ህንዳውያን እና የእሲያ ዝርያ ያላቸው ሰዎች በፋይዘር/ Pfizer፣ ሞደርና/Moderna፣ እና ጆንሰን ኤንድ ጆንሰን/ Johnson & Johnson ክትባት ጥናቶች ላይ ተሳታፊ ሆነዋል። እነዚህ ማህበረሰቦች ከአካል ጉዳተኛ የ LGBTQ+ ማህበረሰቦቻችን ጭምር በአንድ ላይ በአብዛኛው ከመድህኒት ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘት መገለል ብቻም ሳይሆን ያልተቋረጠና ታሪካዊ ዘረኝነት፣ የህክምና ስቃይ እና ጥቃት እንደሚያጋጥማቸው እናውቃለን። እነዚህ ምክንያቶች COVID-19 በእነዚህ ማህበረሰቦች ላይ የሚፈጠረውን ተጽእኖ የሚያባብሰው በመሆኑ ለክትባቱ መስራትና ለሁሉም ሰው አስተማማኝ መሆን ላይ አጽንኦት መስጠት ያስፈልጋል። የህክምና ተመራማሪዎች ክትባቶቹ ለጠቅላላው ህዝብ ጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላም የክትባቶቹ አስተማማኝነት ላይ ቁጥጥር ማድረጋቸውን የቀጠሉት ለዚህ ነው።

## የCOVID-19 ክትባትን መከተብ ያለብዎት ለምንድን ነው?

- **እራስዎን** ከCOVID-19 **ይጠብቁ።**
- **ማህበረሰብዎን ይደግፉ።** ድርጅቶች፣ ትምህርት ቤቶች እና ሌሎች ቦታዎች ክፍት እንዲሆኑ ያግዙ።
- **ክትባቱ ለሁሉም ሰው ነፃ ነው።** የመድን እና የኢሚግሬሽን ሁኔታ ምንም ለውጥ አያመጣም።
- **ወረርሽኙን በማስቆም ላይ ይርዱን።**

### ክትባቱ በውስጡ የሚከተሉት የሉትም

- ክትባቱ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ የሚያደርገው ተጨማሪ የኬሚካል ንጥረ-ነገር የለውም
- የአሳማ ምርቶች ወይም ጀላቲን
- እንቁላል
- ምንም ቫይረስ የለውም

## ክትባቱን ሲከተቡ ምን መጠበቅ አለብዎት



- ክትባቱን በመስጠት ላይ ስልጠና የወሰዱ ሰዎች በሂደቱ ላይ ከእርስዎ ጋር አብረው ይሆናሉ፣ ስለ የትኛውም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች ወይም የጎኒዮሽ ውጤቶች ያወያዩዎታል እንዲሁም ለጥያቄዎችዎ ምላሽ ይሰጡዎታል።
- ለአንዳንድ የCOVID-19 ክትባቶች ከበሽታው ለመጠበቅ የመድህኒቶቹን ሁለት ዶዝ መውሰድ ይጠበቅብዎታል። ክትባቱን የሚሰጥዎ ሰው ሁለተኛ ዶዝ ያስፈልግዎ እንደሆነ እና ይህን መቼ እንደሚወስዱ ይነግርዎታል። ሁለቱም ዶዞቸ የአንድ አይነት ክትባት መሆን አለባቸው። የሚከተቡትየ Johnson & Johnson ክትባትን ከሆነ የሚያስፈልግዎ አንድ ዶዝ ብቻ ነው።
- ለማንኛውም ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ክትትል ይደረግልዎታል።
- ክትባትዎን ሲወስዱ የክትባት ካርድ ይሰጥዎታል። ካርዱ ላይ ምን አይነት ክትባት እንደወሰዱ ይጻፋል።
- ክትባቱን መውሰድ የእርስዎ ምርጫ ነው።



# ክትባቱን ማግኘት የሚችለው ማነው

**ሁሉም በተፈቀዱት የእድሜ ምድቦች ስር የሆኑ የሚኔሶታ ነዋሪዎች የ COVID-19 ክትባትን ለማግኘት ብቁ ናቸው።** ይህ የህክምና ችግሮች ያሉባቸው ሰዎችን፣ ቀደም ሲል በ COVID-19 የተያዙ ሰዎችን እና የተለያየ እድሜ፣ ዘርና የዘር ሀረግ ያላቸው ሰዎችን ያጠቃልላል። ነፍሰ ጡር የሆኑና የበሽታ መከላከያ ስርአታቸው የተዳከመ ሰዎች ክትባቱን ሊከተቡ ይችላሉ። ጥያቄዎች ካሉዎ ዶክተርዎን ያነጋግሩ።

ቀጠሮ ስለማስያዝ የተመለከቱ ፍንጮችን ለማግኘት የ COVID-19 ክትባት ማግኛ ዘዴዎችን በ (www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/vaccine/findvax.pdf ይጎብኙ)።

## የጎንዮሽ ጉዳቶች

አንዳንድ ሰዎች ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ የጎንዮሽ ጉዳቶች አሏቸው። የጎንዮሽ ጉዳቶች ብዙውን ጊዜ አንድ ወይም ሁለት ቀናት የሚቆዩ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ከእለት ተዕለት እንቅስቃሴ አይገድቡዎትም። ሊኖርዎት የሚችለው የሚከተለው ነው፡



የክንድ ህመም



የጡንቻ ህመም



ድካም



ራስ ምታት



ትኩሳት/ብርድ ብርድ ማለት

ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች ካሉዎት፣ ወደ ሆስፒታል ይሂዱ ወይም ወደ 911 ይደውሉ።

## የራስዎን እና ሌሎችን ደህንነት ይጠብቁ

የክትባትዎን የመጨረሻውን ዶዝ ከወሰዱ ከሁለት ሳምንታት በኋላ (በሁለት ተከታታይ ዶዝ ለሚሰጡ ሁለተኛውን ዶዝና በአንድ ዶዝ ለሚሰጥ አንደኛውን ዶዝ) ሙሉ በሙሉ የተከተቡ ተደርገው ይቆጠራሉ። የ COVID-19 ስርጭትን ለመቀነስ ወቅታዊ የማህበረሰብ ጤና መመሪያን በመከተል መቀጠልዎ አስፈላጊ ነው። ሙሉ በሙሉ እስከሚከተቡ ድረስ:



የፊት ጭምብል ያድርጉ።



እጅዎን ይታጠቡ።



ከሌሎች 6 ጫማ ያህል ይራቁ።



ህመም ከተሰማዎ በቤት ውስጥ ይቆዩ።

MINNESOTA

**mn.gov/vaccine**

Minnesota Department of Health | health.mn.gov | 651-201-5000 | 625 Robert Street North PO Box 64975, St. Paul, MN 55164-0975

መረጃውን በሌላ ፎርማት ለመጠየቅ በhealth.communications@state.mn.us ይጻፉ። (Amharic)

5/18/2021